የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

# የትግላችን ግብ የመለስ አገዛዝ ውድቀት ነው!

አርድ አንቀጥቅጥ ሕዝባዊ አመፅን እውን ለማድረግ ሀገር ወዳድ ኃይላት እየጣሩ እየለፉ ያሉት የመለስን አገዛዝ በጥገና ለውጥ አርቆና አለሳልሶ ለማስቀጠል ሳይሆን ከሥር መሠረቱ መንግሎ ለመጣል ነው:: ለዚህም ነው ከመለስ ጋር በመጪው ምርጫ ለመወዳደር ነው ዓላማችን ከሚሉት ጋር ኢሕአፓ አልስማማም ሲል የቆየው::

ሕዝባችን ለዓመፅ ሲነሳ የመጀመሪያና የመጨረሻ ግብ ወይንም ጥያቄዎችን አንግቦ መሆኑ የሚሳት አይደለም:: በመጀመሪያ መፈክሮች ደረጃ "የኑሮ ወድነት ያብቃ!"፤ "ቫት ይሰረዝ!" ፤ "ዋጋ ይቀነስ፤ ደሞዝም ይጨመር!" ፤ "የሀገራችንን መሬት ለባዕዳን መስጠቱና አርሶ አደሩንና ሀገርን መጉዳቱ ያክትም!" ፤ "የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!" ፤ "አፋኝ ድንጋጌዎች ይሰረዙ!" ፤ "የሕዝብ መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበሩ!" ፤ "በሕዝብ ላይ እየተካሄዱ ያሉ ፍጅቶችና አፈናዎች ይቁሙ!" ፤ "የታክሲ ነጂዎችና የሥርቶ አደሩ ጥያቄዎች ምላሽ ያግኙ!"፤ "እህቶቻችንን ለዘመናዊ ባርነት መሸጡ ያብቃ!" ፤ "ሙስና ያክትም፤ በሙስና የተሰማሩት የወያኔ ባለሥልጣኖችም ለፍርድ ይቅረቡ!" ፤ "የሕዝብ ማኅበራት መብታቸው ይከበር!" ፤ "የተለጣፊ ማኅበራት ዕውቅና ያብቃ!" ፤ "በግበረ ሰናይ ድርጅቶችና በነፃው ፕሬስ ላይ የተደነገጉ አፋኝ ሕጎች ይሰረዙ!" ፤ ...ወዘተ፣ ወዘተ፤ የሚሉት መሠረታዊና መነሳትም ያለባቸው አሰባሳቢ ጥያቄዎች ናቸው:: የሀገራችን መሠረታዊ ችግር ምንጩ ግን ዘረኛውና አምባገነኑ የመለስ አገዛዝ ነው:: አገዛዙ በሥልጣን እስካለ ድረስ የሀገርና የሕዝብ መከራ ሊቀነስ ወይም ሊወገድ አይችልም:: ስለዚህም በኢትዮጵያ መብትና ዴሞክራሲን ለማስከበር፤ ሌሎች በሕዝቡ ላይ የተጋረጡ ችግሮችን ሁሉ ለማስወገድ በቅድሚያ የመለስን አገዛዝ በትግል ማሸነፍና መጣል ያስፈልጋል::

በመሆኑም የሕዝባዊው አመፅ ሆነ የትግላችን ግቡ የመለስን አገዛዝ መጣል፣

ማስወገድ መሆን አለበት። ተኪ የለውም ሊሉን ለሚፈልጉት የወያኔ ቅጥረኞችና ሌሎችም መሰጠት ያለበት ምላሽ ይህ አገዛዝ ተወግዶ ሁሉን ሀገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይላት ያቀፈ የሽግግር መንግሥት መመሥረት እንደሚቻል ነው። ስለዚህም የመለስን አገዛዝ በትግል ጥለን ሁሉን ኃይላት የሚያሳትፍ የሽግግር ሂደትን በመከተል ሀገራችንን ወደ ደሞክራሲ ለመውሰድ እንችላለን። የሀገር ቤቱን ትግል በሁሉም አካባቢ በሁለ-ገብ ትግል ማደራጀት፣ መቀስቀስ፣ ማጠናከርና ማታገል የግድ የሚለውም በዚህ ምክንያት ነው።

ለዚህ ግብ እንተባበር! በአመፅ እንነሳ!!
እናቸንፋለን!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France